ሳምንታዊ ዜና

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ -ህዳር 13 ቀን 2001 ዓ.ም.

- በወያኔ ባለስልጣናት መካከል የተጀመረው ፍትጊያ ተቀጣጥሎ ቀጥሏል፤
- መለስ በብአዴንና በኦህዴድ ካድሬዎች ላይ ጣቱን ቀስሯል፤
- ተፈራ ዋልዋና ወርቅነህ ገበየሁ ላይ ምን ተገኝቶ ይሆን?
- የውጭ ምንዛሬ በሀገሪቱ ሙሉ ለሙሉ በመጥፋቱ ፋብሪካዎች እያቆሙ መሆኑ ተነገረ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ ሹም ሽረቱ ተጧጥፎ ቀጥሏል፤
- ከ200 በላይ ባለስልጣናት በአንድ ቀን ከስልጣናቸው ተባረሩ፤
- የክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስኪያጅ የወር ደመወዝ ከ5500 ብር በላይ ሆኖ ተመደበላቸው፤
- ኩማ ደመቅሳን የሚቆጣጠሩ የደህንነት ኃይሎች ተመደቡ፤
- ጃፓን በነፃ ለህዝቡ እንዲሰጥ ያቀረበችው ስንዴ ኩንታሉን በ350 ብር ወያኔ መቸብቸብ ጀመረ፤
- በኦሮሚያም ሹም ሽረት ተደረገ፤
- የኦሮሚያ ምክር ቤት አባሎች ያነሱት ጥያቄ ውድቅ ሆነ - ማስጠንቀቂያም ተሰጣቸው፤ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

በወያኔ ቡድን መካከል ከፍተኛ ሽኩቻ ተፈጥሮ ከዕለት ወደ ዕለት እየተካረረ መምጣቱንና ለአንዳንድ ባለስልጣናት መገለል ምክንያት እንደሆነም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::

በተለይ ከምርጫ 1997 ዓ. ም. በሁዋላ በሀይል ስልጣኑን አጠናክሮ የቀጠለው ወያኔ ከህዝብ በደረሰበት ከፍተኛ ጥላቻ የተነሳ በባለስልጣናቱ መካከል « አንተ ነህ ለዚህ ውድቀት የዳረግከን ፤ አንተ ነህ» እየተባባሉ እርስ በርስ የጀመሩት ንትርክ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መጥቶ ዛሬ ለከፍተኛ ችግር እንደዳረጋቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገልፆዋል::

በብአዴንና በኦህዴድ ካድሬዎች ዘንድ የሚነሱ ጥያቄዎች እና ለኛም ስልጣን ይገባናል የሚል ሀሳብ መሰንዘራቸው የራስ ምታት የሆነባቸው ህወሀቶች የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ የተለያዩ ዘዴዎች ቢጠቀሙም ነባር ናቸው የተባሉት ጭምር የሚያነሱዋቸው ተቃውሞዎች አስደንጋጭ እንደሆነባቸው የገለፁት ምንጮች ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ሲንከባለል የመጣው ተቃውሞ ዘንድሮ በጥቂት ካድሬዎች ላይ የሹም ሽረት እርምጃ መወሰድ መጀመሩን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በ2000 ዓ. ም. መጨረሻ ላይ አራቱም የወያኔ ድርጅቶች የተናጠል ስብሰባ ባደረጉበት ወቅት የተነሱት ጥያቄዎች ተመሳሳይነት ያላቸው ከመሆኑም ባሻገር በአንዳንድ ነባር ካድሬ ባለስልጣናት ዘንድ ለውጥ መፈለግ መታየቱ እነ መለስን ያስደነገጠ በመሆኑ እርምጃ እንዲወስዱ ምክንያት እንደሆናቸውም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

«ስልጣንና ሀብት የግል ነው» እያሉ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና ጥቂት የወያኔ ባለስልጣናት ሙጭጭ ብለው የቆዩ ቢሆንም ተፈራ ዋልዋ ከመለስ ጋር ባለው ውስጣዊ ግጭትና ንትርክ ቀስ በቀስ ከስልጣኑ ለመነሳት እና ለመነጠቅ ምክንያት እንደሆነ የገለፁት ምንጮቹ በተለይ በብአዴኖች ላይ ከረርና መረር ያለ እርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑንም አስረድተዋል::

በነሀሴ ወር በመለስ ብጣሽ ወረቀት ትዕዛዝ ከብአዴን ምክትል ሊቀመንበርነቱ የተነሳው ተፈራ ዋልዋ በአዋሳው ጉባኤ ላይ ከመለስ ጋር ሙግት ገጥሞ በቃላት ሲፋለም የነበረ ቢሆንም ሰሞኑን መለስ ጊዜ ጠብቆ በሙስና ሰበብ ዘብጥያ ሊያወርደው መዘጋጀቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ዘገባ ያስረዳል::

በተፈራ ላይ የተጀመረው የውንጀላ ዘመቻ ከባህር ዳር ጉባኤ ጀምሮ እስከ አዋሳው ድረስ « ከስልጣን ለቀን ለአዲሱ ትውልድ እናስረክብ» የሚል አቋዋም በመያዙና በይፋ በመከራከሩ መለስን ከማናደዱና ከማበሳጨቱ በተጨማሪ አንገቱን ያስደፋ በመሆኑ ከበረከት ጋር በመሆን የሚቀብርበትን ጉድጉዋድ ሲምስ ቆይቶ በቅርቡ ህልምና ምኞቱን እውን ለማድረግ እየተሩዋሩዋጠ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ከአዲስ አበባ

መስተዳድር ከንቲባነት እስከ መከላከያ ሚኒስትርነት ብሎም አቅም ግንባታ ድረስ ባሉት ጊዜያት የሰራቸው ግድፈቶች እየተለቀሙ ጥራዝ እየተሰሩ መሆናቸውንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

እንደ ጣኦት እያመለኩት መለስ ያለውን እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋቡ ሲለፍፉ የነበሩት ብአዴኖች ቂጭ ብለው የሰቀሉትን ቆመው ማውረድ ተስኖዋቸው በቁጭት እያነቡ ሲሆን መፍትሄ  ካለማግኘታቸውም በላይ በወረንጦ እየተለቀሙ መሆናቸውን የገለፁት ምንጮች ህላዊ ዮሴፍን ሙሉ ለሙሉ ከፖለቲካ እና ከስራ ውጭ፤ ተፈራ ዋልዋን ከፓርቲው ምክትል ሊቀመንበርነት አባርሮ አሁን ደግሞ በሙስና ሰበብ ዘብጥያ ለማውረድ ድራማ እየተዘጋጀለት ሲሆን የብአዴንን ደካማ ጎን እያነፈነፈ አከርካሪውን በመምታት መለስ እንዳሻው እንዲፈነጭበት በረከት የተባለውን የጋሪ ፈረስ ተጠቅሞ እየጋለበ  ከመሆኑም ባሻገር የብአዴን ሊቀመንበር የአዲሱ ለገሰን ስልጣን በእጅ አዙር ውስጥ ውስጡን በረከት እንዲቆጣጠር መደረጉንም  ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በተፈራ ላይ የተጀመረው የሙስና ሰበብ በቅርቡ ከግልገል ጊቤ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ የኃይል ማመንጫ ግንባታ ጋር በተያያዘ ብዙ ሚሊዮን ብር ምዝበራ ተፈጽሞዋል በሚል ግለሰቡን በቁጥጥር ስር የማዋል እርምጃ ሊወሰድ ይችላል ያሉት ምንጮች አሁን የተጀመረው እንቅስቃሴ ወደ ሌሎችም ባለስልጣናት ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል ስጋታቸውን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በፖሊስ ኮሚሽነሩ የኦህዴዱ ካድሬና ደህንነት ወርቅነህ ገበየሁ ላይም ቀይ መብራት የበራበት በመሆኑ በሱም ላይ የሚያጠነጥን  የሙስና ወንጀል መኖሩን ምንጮቹ ጠቁመው ፖሊስ ገለልተኛና ከፖለቲካ ነፃ መሆን አለበት በማለት ወያኔ ባወጣው ህገ መንግስት ተብዬው ላይ ያሰፈረ ቢሆንም  እራሱ ያወጣውን ህግ ንዶና አፍርሶ ወርቅነህ ገበየሁን የወያኔ የምክር ቤት አባል እንዲሆን ተደርጎ እየሰራ ከመሆኑም በተጨማሪ አጫጭር የደህንነት ኮርሶችን  በአሜሪካ፤ በእንግሊዝና  በጀርመን እንዲወስድ ተደርጎ ኦህዴድ ውስጥ ያሉትን ባለስልጣናት እንዲሰልል የተመደበ ቢሆንም ዛሬ ግን መልሶ እሱ እራሱ ሌላ ሰላይ ተመድቦበት ውሎውና አዳሩ ሳይቀር እየተጠና መሆኑን እና በቅርቡም  እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል ሲሉ ምንጮቹ ስጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

በኦህዴድና በብአዴን ላይ ያነጣጠረው የመንጥር ዘመቻ ከአፈንጋጭ ቡድን ጋር ግንኙነት አላቸው በተባሉ ጥቂት የህወሀት ባለስልጣናትም ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወሰድ  ይችላል ያሉት ምንጮቹ ዙሪያውን በፖለቲካ ቀውስ ውስጥ የተዘፈቀው መለስ ግራ ተጋብቶ መወሰን ተቸግሮ እንዳለም  አስረድተዋል፡፡

አማካሪ፤ አዛዥና ተቆጪ ሆና መለስን እያስከረከረችው ያለችው አዜብ መስፍን ባሉዋ የፖለቲካ ኪሳራ ውስጥ ገብቶ እየዳከረ መውጫ አጥቶ እያየችው በእሳት ላይ ቤንዚን እንዲሉ እያርከፈከፈች መገኘትዋ አስገራሚ ነው ሲሉ ምንጮቹ ገልፀዋል::

ዛሬ የሀገሪቱ ህዝቦች ችጋርና የኑሮ ውድነት የስንግ ይዞዋቸው ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት ከዓለም ላይ የደሀዎች ደሀ መሆኑን የዓለም ህዝብ ሳይቀር እያወቁ ሽምጥጥ አድርገው ክደው « በኛ አመራር የመጣ ልማት ነው» እያሉ ማቅራራታቸው የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ መሆናቸውን ያሳያል ያሉት የአራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ መምህር በሱማሊያ ውስጥ ሳይቸግራቸው ገብተው እየዳከሩ የደረሰባቸው ኪሳራ ሳያንስ አሁን ደግሞ ጦሩን እንኩዋን ለማውጣት አቅቶዋቸው የድረሱልን ጥሪ እያሰሙ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ በድል ጎዳና ላይ ነን እያሉ መወትወታቸው አሳዛኝ እና አሳፋሪ በሬ ወለደ ብለው መናገር የሚደፍሩ ማሰቢያ የሌላቸው ድውዮች ናቸው ሲሉም በንዴት ገልፀዋል::

ረሀብና የኑሮ ውድነት እያሰቃየው ያለው ህዝብ ችግሬ ከዛሬ ነገ ይቃለላል እያለ በተስፋ እየተጠባበቀ ባለበት በዚህ ወቅት የውጭ ምንዛሪ በሀገሪቱ ባለመኖሩ በርካታ ፋብሪካዎች እየተዘጉ ሰራተኛውን እያሰናበቱ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ሙሉ ለሙሉ በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንክ ውስጥ አንድም የውጭ ምንዛሪ የሌለ በመሆኑ ነጋዴዎች ጥሬ እቃ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከመቸገራቸውም በላይ በሀገር ውስጥ የተሰማሩበት ስራ በመቆሙ ሀገሪቱ ወትሮ ከነበረችበት ችግር የባሰ አዘቅት ውስጥ እየገባች መሆኑን አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ነዳጅ በዓለም ላይ ከ50 ዶላር በታች እያሽቆለቆለ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ግን በሚገርም ፍጥነት እያሻቀበ ከመሆኑም በተጨማሪ ነዳጁን መግዣ የውጭ ምንዛሪ ስለሌላቸው በነዳጅ እጥረት ህዝቡ እየታመሰ መሆኑንም ዘገባው አስረድቶዋል::

በብድር እና በእርዳታ የሚመጣውን የውጭ ሀገር ገንዘብ በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ስም እየቦጠቦጡ በውጭ ሀገር ባንኮች ውስጥ እያከማቹ ሀገሪቱዋን ባዶ በማስቀረታቸው የንግዱ ህብረተሰብ የንግድ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ መገደቡን እና ብዙ ፋብሪካዎች ለመዘጋት እንደተገደዱ ለመረዳት ተችሎዋል ሲል ዘገባው አብራርቶዋል::

በአዲስ አበባ ምክር ቤት እና በኦሮሚያ ምክር ቤት በተባሉ የወያኔ ተቀፅላ መስተዳድሮች ውስጥ ሹም ሽረቱ እንደቀጠለ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከተሾሙ ወራትን እንኩዋን ያላስቆጠሩት አዲሶቹ የወያኔ ካድሬዎች ምክንያቱ በግልፅ ባልታወቀ ሁኔታ ከስልጣናቸው መባረራቸውን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል።

ከህዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሆነው የማባረሩ ዘመቻ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ 99 ቀበሌ ዋና ስራ አስኪያጆች እና 99 የቀበሌ መሬት አስተዳደር መሆናቸውን እና በምትካቸውም ሌሎች አፍለኛ ካድሬዎች መመደባቸውን ዘገባው አስረድቶዋል።

ከህዳር 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ከስልጣናቸው እንዲነሱና እንዲንሳፈፉ የተደረጉት የቀበሌ ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ስራ አስኪያጅ ታምራት የተባለው ግለሰብ ፤ የማስታወቂያ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዮሐንስ አንዳርጌ ፤የመሬት አስተዳደር ምክትል ኃላፊን ጨምሮ ሌሎችም መባረራቸውን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

ከባለ አደራው አስተዳደር ከ4 ወር በፊት የተረከበው የቀድሞ መከላከያ ሚኒስትር የአሁኑ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የኩማ ደመቅሳ ካቢኔ ገና ከጅምሩ በሹም ሽር እየናጠው ከመሆኑም ባሻገር በተለይ በስራው ላይ የነበሩ ናቸው የተባሉት ካድሬዎች ሙሉ በሙሉ ከስልጣናቸው እንዲባረሩ መደረጉን ዘገባው አስረድቶዋል።

ከአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እስከ ቀበሌ ድረስ ከ200 በላይ ባለስልጣናት በአንድ ቀን በኩማ ደመቅሳ ፊርማ የተሰናበቱ ሲሆን፤ በምትካቸው ለአንድ ወር በሻሸመኔ ከተማ በሚገኘው አላጌ ግብርና ኮሌጅ ውስጥ ሲሰለጥኑ ከነበሩት 2 ሺህ ካድሬዎች ውስጥ እየተመረጡ መሾማቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በተለይ በምርጫ ተወዳድረው የነበሩትን ካድሬዎች ሙሉ ለሙሉ ከስልጣን የባረሩዋቸው መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል።

በቅርቡ ወያኔ ብቻውን ተወዳድሮ አሸነፍኩ ያለበት ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ በገንዘብና በጥቅማጥቅም ይዘዋቸው የነበሩትን ሆድ አደር ግለሰቦች እያባረረ ነባርና በረሀ አመጣሽ ካድሬዎች በየቦታው እየሰገሰገ ሲሆን ከምክር ቤቱ ውስጥ ብቻ ከ12 ባለስልጣናት በላይ እንደተባረሩ ለማወቅ ተችሎዋል ሲል የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

ህዝቡ የዕለት ጉርስ የሚቀምሰው አጥቶ የአምላክን እርዳታና ድጋፍ እየጠበቀ ባለበት በዚህ ወቅት አዲስ ለተሾሙት የክፍለ ከተማ ስራ አስኪያጆች ናቸው ለተባሉ ካድሬዎች የወር ደሞዝ ከነ አበላቸው ተብሎ ከ5 ሺህ ብር በላይ እንደተመደበላቸው ዘገባው ገልፆ ያለምንም ስራ ወንበር ሲያሞቁ ለሚውሉት ሆድ አደር፤ ስግብግብ ካድሬዎች የወር ደመወዝ 4200 ብር እና ለነዳጅ ፤ ለቢሮ አበልና ለሻይ ቡና በሚል ከ1500 ብር በላይ በአጠቃላይ በወር ከ5500 ብር በላይ የሚከፈላቸው ሲሆን፤ ከህዝብ

ላይ የሰበሰቡትን ሀብት እርስ በርስ እያውካኩ  እየተቦጫጨቁ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

በቅርቡ በሆዳቸው ተደልለው ለምርጫ ገብተው ለ3 ወር ጊዜ ብቻ  ስልጣን ላይ እንዲቀመጡ የተደረጉት እነዚሁ ተባራሪ  ካድሬዎች በነመለስ ዘንድ አመኔታ ስላላገኙ ከስልጣናቸው ሊባረሩ እንደቻለና አሁን የተጀመረው  ምንጠራም ቀጣይ እንደሆነም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ስማቸውን ሲጠየቁ የውሽሞቻቸውን ስም የሚናገሩ ሁለት እጃቸው ግራ የሆኑነት እነዚሁ ሆድ አደር  ካድሬዎች የህዝቡን ጉሮሮ ዘግተው ሁሉን ለራሴ እያሉ የሚስገበገቡ ሲሆን በእርዳታ የመጣውን እህል እንኩዋን በብር እየሸጡ መሆናቸው አሳዘኝ ነው ሲሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት ግራ ተጋብተው አንዴ ሲሾሙ ሌላ ጊዜ ሲሽሩ ጊዜያቸውን በሹም ሽረት እየጨረሱ የሚገኙት እነ ኩማ ደመቅሳ ህዝብ አንቅሮ የተፋቸው መሆኑን እያወቁ ለማስመሰል ያህል አንዱን እያነሱ  ነባርና ታማኝ የሆኑትን  ካድሬዎች ቢሾሙም ለህዝቡ አንዳችም ፋይዳ የለውም ያሉት  የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ  ዛሬ የህዝቡ ጥያቄ ዳቦ መሆኑን እያወቁ  እነሱ እርስ በርሳቸው እንደ ጆፌ አሞራ ሲናከሱ መታየታቸው የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያሳፍር ነው ሲሉ ተችተዋል፡፡

ለአዲስ አበባና ለሌሎችም ክልሎች ለተጎዳው ህዝብ እርዳታ የሚሆን ብዙ ሜትሪክ ቶን ስንዴ የጃፓን መንግስት በነፃ የሰጠ ቢሆንም የነመለስ ቡድን ያለ አንዳች ሀፍረት እና ይሉኝታ ኩንታሉን በ350 ብር ሂሳብ የእህልን ዋጋ ለማረጋጋት እየሸጥን ነው እያሉ መግለፃቸው ህዝቡን ንቀው መሆኑን ያሳያል ያለው ዘገባው ህዝቡ የሚቀምሰው ባጣበት በዚህ ወቅት  ቢቻል ከመንግስት ካዝና ገንዘብ ወጭ አድርገው ገዝተው ለተቸገረው ወገናችን መስጠት ሲገባቸው በእርዳታ በነፃ የመጣውን እህል በገንዘብ እየቸበቸቡ ለራሳቸው የወር ደመወዝ በሚል ከ5 ሺህ ብር በላይ ማግበስበሳቸው  የሚገርም ታሪክ ነው ሲል ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

ለ3 ዓመታት በባለ አደራው አስተዳደር በአቶ ብርሀኑ ደሬሳ ከንቲባነት ሲመራ የቆየው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በ1997 ዓ. ም. ወያኔዎች ሆን ብለው በፈጠሩት ግር ግር ምክንያት በወቅቱ ለተመረጡት ሳይሰጡ በመቅረታቸው መለስ እራሱ አዋቅሮ የሾማቸው ሲሆን ፤ በነሀሴ 2000 ዓ . ም. ስራውን አጠናቅቆ ብቻቸውን ተወዳድረው ብቻቸውን አሸነፍን ላሉት ለነ ኩማ ደመቅሳ የተሰጠ ቢሆንም ገና ወራት ሳያስቆጥሩ ሹም ሽረቱ እየተጡዋጡዋፈ መሆኑ የወያኔ ቡድን እየተዳከመ መሆኑን ያሳያል ሲሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ  45 ኪሎ ሜትር ርቀት ድረስ ያሉትን ከተሞች የጠቀለለው የመለስ አገዛዝ ለወያኔ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገቡ መሆናቸው በጥናት

የተደረሰበት በመሆኑ ወደ አዲስ አበባ ስር ለማስገባት እንደቻሉ የገለፀው ዘገባ ሙሉ ለሙሉ የተጠቃለሉት የኦሮሚያ ክልሎች በመሆናቸው እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ በመስተዳድሩ ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን እንዲይዙ የተደረጉት የኦህዴድ ካድሬዎች ይሁኑ እንጂ የበላይ ተቆጣጣሪው መለስ ዜናዊ ከስር ደግሞ የደህንነት ባለስልጣናት መሆናቸውንም አብራርቶዋል::

በዚህም መሰረት ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ኦህዴድ፤ የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊው ዳባ ደበሌ ኦህዴድ ፤የከንቲባው ፅህፈት ቤት ኃላፊ ከቡራዩ ከተማ ሊቀመንበርነት ተነስቶ የመጣ ሞቱማ መቃሳ የተባለ ግለሰብ ኦህዴድ፤ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፍቃዱ ቶሌራ ኦህዴድ እና ሌሎችም ቁልፍ ቦታዎችን የያዙ ቢሆንም ለይምሰል የተቀመጡ ካልሆነ በስተቀር የመወሰን አቅማቸው ደካማ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል::

በተለይ ዳባ ደበሌ የተባለው ሆድ አደር ግለሰብ ወያኔ ወደ ስልጣን ሊወጣ በተቃረበበት ወቅት በጅማ ከተማ ውስጥ የቡና ቤት አስተናጋጅ ሆኖ ሲሰራ የነበረና በ1983 ዓ.ም. ተቀላቅሎ የ3ወር ስልጠና ተሰጥቶት የምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳዳሪ ሆኖ ሲያገለግል እንደቆየና የኦህዴድ እና የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እንደነበረ አስረድተዋል::ከ6 ወር በፊትም የቡራዩ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ህዝቡን ልታሳምፅ ነው በሚል ያለስራ ለብዙ ጊዜ እንዲቀመጥ ተደርጎ እንደነበረና አሁን የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሲቁዋቁዋም በአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ ሆኖ እንደተሸመም ለማወቅ ተችሎዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መሰረታዊ የህዝብ ችግሮች ስር ሰድደው ባለበት ወቅት ወያኔዎች ሁሉን ለራሴ በሚል ብቻ እየተስገበገቡ መሆናቸው ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዲፕሎማቶች ሳይቀር ጠንቅቀው ያወቁት ጉዳይ ነው ያሉት ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች በአለም ላይ ነዳጅ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ረክሶ ነዳጅ ሻጭ ሀገሮችን ግራ እያጋባ ባለበት ወቅት እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ነዳጅ ጠፍቶ አሽከርካሪዎች ተቸግረው እየተጉላሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ዲፕሎማቶችም ብዙ መኪኖቻቸው በነዳጅ እጥረት የተነሳ እንደልባቸው ማንቀሳቀስ ተስኖዋቸው ለማቆም እንደተገደዱ እያወቁ አንዳችም መፍትሄ ለመስጠት ያልቻለው የኩማ ካቢኔ አቅመ ቢስ መሆኑን በግልፅ ያሳየበት ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በምሬት እየገለፁ ናቸው::

በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉትን ከፍተኛ ገቢ ሲያስገቡ የነበሩትን ከተሞች እነ መለስ ጠቅልለው ካስገቡ በሁዋላ ለይምሰል እና ህዝቡን ለማታለል በአዲስ አበባ ምክር ቤት ውስጥ የኦሮሞ የበላይነት አለ ለማሰኘት ድራማ እየሰሩ ቢሆንም የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ እያገለገለ ያለው መለስ ዜናዊ ሲሆን ከስር ደግሞ ነባር የህወሀት በረሀ አመጣሾች

የደህንነትና የፖለቲካ  ካድሬዎች ተሰግስገው እነ ኩማ ደመቅሳን የሚቆጣጠሩ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

በሀገር ውስጥና በውጭ የስንግ ተወጥሮ ያለው የወያኔ ቡድን  በውስጡ ባለበት ችግር የተነሳ የራሴ ናቸው የሚላቸውን የኦህዴድና የብአዴን  ካድሬዎች  በአይነ ቁራኛ እየጠበቀ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉ የብአዴን ነባር ታጋይ የነበሩትን ከስልጣን እያገለላቸው እንደሚገኝም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በኦሮሚያ ተብሎ በወያኔ የተሰየመው ክፍል ውስጥም ከፍተኛ የሹም ሽረት እየተካሄደ መሆኑን ከናዝሬት የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡ የደርግ ወታደር ሆኖ ሲሰራ የነበረው እና ተማርኮ ለወያኔ   ታጋዮች የውሀ ጀሪካን አመላላሽ የነበረው ጄኔራል አባዱላ ገመዳ በሁዋላም ስልጣኑን በመለስ ዜናዊ ተነጥቆ አቶ በተባለው አባዱላ ገመዳ  የሚመራው ኦሮሚያ የተባለው ክልል ካድሬዎቹን  እያነሳና እየጣላቸው መሆኑን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

የውስጥ ችግሮቻቸውን በመሸምና በመሻር የሚያቃልሉ እየመሰላቸው   ዛሬ ስልጣን ላይ ያስቀመጡትን   መልሰው እያነሱ በሌላ እየተኩ  መሆኑን የገለፀው ዘገባ የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንት   የነበረውን ሙክታር ከድር የተባለውን ካድሬ አንስተው የኩማ ደመቅሳ የፅህፈት ቤት ኃላፊ የነበረውን አብዱላዚዝ አህመድ የተባለው በቦታው መተካቱን ዘገባው አብራርቶዋል፡፡  አብዱላዚዝ አህመድ የተባለው የወያኔ ካድሬ  ትውልዱ ዓለማያ ሲሆን በ1997 ዓ. ም. ሽግግር ወቅት የድሬዳዋ መስተዳድር ከንቲባ ሆኖ  ሲያገለግል የነበረ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንትነት የተነሳው ሙክታር ከድር የተባለው በኃይለማሪያም ደሳለኝ ምትክ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የህዝብ አደረጃጀት አማካሪ ሚኒስትር ፤ ሽፈራው ጃርሶ በጠቅላይ ሚኒስትር የተፋሰስ ጉዳዮች ሚኒስትር ተደርገው የተሸሙ መሆኑን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡ እነዚህ አማካሪ ተብለው የተሸሙት ሁለት የኦህዴድ  ካድሬዎች ከድርጅቱ ተቃውሞና ኩርፊያ እንዳያስከትል መለስ ስለሰጋ ብቻ አስቀመጣቸው እንጂ አንዳችም ስራ የሌላቸው ወንበር ሲያሞቁ ውለው እንዲመለሱ ሆን ተብሎ የተሰጣቸው ቦታ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

በህዝብ ብዛት እኛ መሆናችን እየታወቀ ፤ ለሀገሪቱም ከፍተኛ ገቢ የምናስገባው እኛ መሆናችን እየታወቀ የህወሀት የበላይነት እስከ መቼ ሊቀጥል ይችላል? እያሉ የኦህዴድ አዳዲስ    ካድሬዎች በተለያዩ የስብሰባ ቦታዎች ጥያቄ እያነሱ በማስቸገራቸው እየተበሳጨ የነበረው መለስ በቅርቡ የሚኒስትሮች ሹም ሽረት ሲያደርግ ጥቂት ወጣት ሚኒስትሮችን ለማስመሰል የሾመ ቢሆንም አሁንም ውስጥ ውስጡን ኦህዴድ በተባለው የወያኔ ጀሌ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ፍትጊያ መኖሩን ከናዝሬት የደረሰን ዘገባ ገልያዋል፡፡

በተለይ ባለፈው ሳምንት ሹመት ለመስጠትና ለመንፈግ ስብሰባ ናዝሬት ከተማ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው የኦህዴድ ምክር ቤት ውስጥ « በአሁኑ ሰዓት ወገኖቻችን ያለ አንዳች ጥፋት የኦነግ አባል ናቸው ፤ ሽብርተኛ ናቸው እየተባሉ ከያሉበት ቦታ እየተለቀሙ ለእስር ሲዳረጉ ይህ ምክር ቤት ምንም የወሰደው እርምጃ የለም» በማለት ብዙዎቹ ጥያቄ እና ሀሳብ ቢያቀርቡም ሀሳባቸው ተቀባይነት ከማጣቱም በተጨማሪ ይህንን ጥያቄ ያቀረቡት የምክር ቤት አባሎች ክትትል እንዲደረግባቸውና አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው አባዱላ ገመዳ ትዕዛዝ መስጠቱን ከስብሰባው ተሳታፊ ከነበሩ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በአባዱላ ትዕዛዝ የተበሳጩት አንዳንድ የምክር ቤት አባሎች ለምን ይህንን ትዕዛዝ እንዳስተላለፈ ለብቻው ሲጠይቁት ከእኔ ጀርባ የተሰገሰጉ ኦሮሚኛ ተናጋሪ የወያኔ ደህንነቶች ስላሉ እራሴን ለማዳን የወሰድኩት እርምጃ ነው ሲል ምላሽ መስጠቱን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ እና በሌሎችም የኦሮሚያ ከተሞች ውስጥ ውጥረቱ ሰፍኖ ነጋዴው ፤ የመንግስት ሰራተኛው፤ መሀንዲሱ እና ሌላውም አካል ምን ይደርስብኝ ይሆን በሚል ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንዳሉም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በናዝሬት ከተማ ውስጥም ተመሳሳይ የማተራመስ ስራ እየተሰራ ሲሆን በተለይ በመሀንዲሶች እና ፕላን አንሺዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ከመደረጉም በላይ ስራቸውን በነፃነት እንዳይሰሩ እየተደረገ እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከተማዋን በፌዴራል ስር ለማድረግ ውስጥ ውስጡን ሴራ እየተውጠነጠነ መሆኑን የጠቀሱት አንዳንድ የምክር ቤቱ ሰራተኞች በተለይ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ በመሆኑ ናዝሬትም ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያሳየች ያለች ከተማ በመሆኑዋና ከፍተኛ ገቢ ያላት በመሆኑዋ ይህንኑ ገንዘብ እነመለስ ለመቀራመት አስበው ወደ ፌዴራል ስር ለማስገባት ውስጥ ውስጡን እያውጠነጠኑ መሆናቸውን ዘገባው አብራርቶዋል:: ለመቆጣጠር እንዲያመች በሚል ቀድሞ 14 ቀበሌዎች የነበራት ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 02 የተባለው ተቀርጦ ለገበሬ ማህበር እነደተሰጠና ቦኩ ሸነን ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተብሎ ስያሜ እንዳገኘ ከደረሰን ዘበገባ ለማወቅ ተችሎዋል::